Amharic

# የጭስ ማስጠንቀቂያ ደወል

**ቪክቶሪያ ውስጥ ባለው ህግ መሰረት ለነዋሪዎች ንብረቶች በሙሉ ቢያንስ አንድ የጭስ ማስጠንቀቂያ ደወል በእያንዳንዱ ህንጻ ደረጃ ላይ መገጠም አለበት።**

**MFB እና CFA የሚመከረው በጥንቃቄ እና በጥብቅ የተከለለ እና ጭስን እንዳለ የሚጠቁም የጭስ ማስጠንቀቂያ ደወል ለ10-ዓመታት ከሚሰራ ሊቲየም ባትሪ ጋር**

- ጭስ እንዳለ የሚጠቁሙ የማስጠንቀቂያ ደወሎች ስኬታማ ናቸው ብሎም ለውሸት  ማስጠንቀቂያ የተጋለጡ አይደሉም፡
- እነዚህ ለብቻቸው መቆም ይችላሉ (ከ 240v ቮት ካለው ዋና ኤሌትሪክ ምንጭ ሃይል ጋር አይቀጠሉም) ወይንም ከሃይል መስጫ- ሽቦ/hard-wired (ከ240v ቮት ካለው ዋና ኤሌትሪክ ምንጭ ሃይል ጋር ይቀጠላል)።







## በየወሩ መፈተሽ

- ቁልፉን መጫን
- ሶስት ጊዜ የማስጠንቀቂያ ድምጽ እስኪሰማ ድረስ ቁልፉን በመጫን መቆየት

## በየዓመቱ አቧራን ማራገፍ

- በጭስ ማስጠንቀቂያ ደወል ዙሪያ ያለውን ሽፋን ቀስ አድርጎ አቧራን ማራገፍ ወይም መጥረግ

* ተግባራዊ ከሆነ የጭስ ማስጠንቀቂያ ደወልዎን ባትሪ መቀየር

## በየ 10 ዓመታት መቀየር

- የጭስ ማስጠንቀቂያ ደወል በሙሉ (ለሃይል መስጫ-ሽቦ/hard-wired እና በራሱ የቆመን) መቀየር አለበት

# የእኔን ማስጠንቀቂያ ደወል የት ላይ ነው የሚገጠመው?

- የጭስ ማስጠንቀቂያ ደወል የሚገጠሙት ከግድግዳ ቢያንስ 30 ሴ.ሜትር እርቀት ባለው ጣራ ላይ መሆን አለበት።
- የጭስ ማስጠንቀቂያ ደወል በእያንዳንዱ የመኝታ አካባቢና በሌላው የቀረው የቤት ቦታ መካከል ላይ መሆን አለበት።
- አንድ ሰው በሩን ዘግቶ በሚተኛበት ማንኛውም ክፍል ውስጥ የጭስ ማስጠንቀቂያ ደወሎች መኖር አለባቸው።
- የጭስ ማስጠንቀቂያ ደወሎች የአውስትራሊያን ደረጃ AS3786 ማሟላት አለባቸው።

Certified Product™
Australian Standard

■ በመኝታ አካባቢና በሌላው የቀረው የቤት ቦታ መካከል ላይ መገጠም አለበት።

● ተጨማሪ መከላከያ ለማድረግ የጭስ ማስጠንቀቂያ ደወል መገጠም ሊኖርበት የሚችል ተጨማሪ ቦታዎች

